የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች
# ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት
# የ2011 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲትሪፖርት

መጋቢት/2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች**

**ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት**

**የ2011 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት**

የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የተመደበለትን በጀት በፋይናንስ አዋጅ ፣ ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሃብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2011 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርቶች እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢንስቲቲዩቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ/የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ኢንስቲቲዩቱ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኢንስቲቲዩቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኢንስቲቲዩቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ሪፖርት
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት
- የሂሣብ ማመዛዘኛ ሪፖርት
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣</u>

ኢንስቲትዩቱ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

1. ደጋፊ ማስረጃ ያልቀረበለት የውጭ ጉዞ አበል ክፍያ ብር56,359.07 ተገኝቷል፡፡
2. የዋጋ ማወዳደሪያ ያልቀረበለት የአገልግሎት ግዥ ብር 280,964.60 ተገኝቷል፡፡
3. ከበጀት ዓመቱ ውጭ የተፈጸመ ክፍያ ብር 51,925.60 ተገኝቷል፡፡
4. ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ የሙያ አበል 20,000.00 ተገኝቷል፡፡
5. ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ ብር 630,925.14 ተገኝቷል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 5 ከተገለጹት በስተቀር በእኛ አስተያየት የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30/2011ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ፣ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ፡፡

<u>ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች</u>

6. ያለአግባብ የተከፍለ ውሎ አበል ክፍያ ብር 3,543.00
7. በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ብር551,805.45
8. ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት ብር 42,914,407.35 (47.73%) ተገኝቷል፡፡

ከሠላምታ ጋር

---------------

**ደመቀች ሞገስ**

**የፋይናንሻል ኦዲት ሥራ አስኪያጅ**

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
የዕቅድና ግዢ ... (stamp)